አንቀጽ ፡ ፶፰ ።

እስመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይትመዐዕ ፡ ላዕለ ፡ እኁሁ ፡ በከንቱ ፡ ደለወ ፡ ላዕሌሁ ፡ ኵነኔ ። ወዘይቤሎ ፡ ለእኁሁ ፡ ርሱሕ ፡ ዘፀርቅ ፡ ደለዎ ፡ ነውረ ፡ ማኅበር ። ወዘሂ ፡ ይቤሎ ፡ ለእኁሁ ፡ ዓብድ ፡ ደለዎ ፡ እሳተ ፡ ገሃነም ። ለእመ ፡ አንተ ፡ አምጻእከ ፡ መባአከ ፡ ኀበ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወተዘከርከ ፡ በሀየ ፡ ከመ ፡ ቦ ፡ እኁከ ፡ ዘተኀየሰከ ፡ ኅድግ ፡ ህየ ፡ መባአከ ፡ ቅድመ ፡ ምሥዋዕ ፡ ወሑር ፡ ቅድመ ፡ ወተዐረቅ ፡ ምስለ ፡ እኁከ ፡ ወእምዝ ፡ ገቢአከ ፡ አብእ ፡ መባአከ ።

፩ሺ፮፻፮ ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ ለቀደምት ፡ ኢትዘምዉ ፡ ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ኵሉ ፡ ዘርእያ ፡ ለብእሲት ፡ ወፈተዋ ፡ ዘመወ ፡ ባቲ ፡ በልቡ ። ተብህለ ፡ ዘይድኅራ ፡ ለብእሲቱ ፡ የሀብ ፡ ላቲ ፡ መጽሐፈ ፡ ኅዳጋቲሃ ፡ ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ዘይድኅራ ፡ ለብእሲቱ ፡ ዘእንበለ ፡ ነገረ ፡ ዝሙት ፡ ለሊሁ ፡ ረሰያ ፡ ዘማዊተ ፡ ወዘሂ ፡ አውሰባ ፡ ኅድግተ ፡ ናሁ ፡ ዘመወ ።

፩ሺ፮፻፯ ወካዕበ ፡ ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ ለቀደምት ፡ ኢትምሐል ፡ በሐሰት ፡ ወአግብእ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መሐላከ ። ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ኢትምሐሉ ፡ ግሙራ ፡ ኢ ፡ በሰማይ ፡ እስመ ፡ መንበሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ውእቱ ፡ ወኢ ፡ በምድር ፡ እስመ ፡ መከየደ ፡ እገሪሁ ፡ ይእቲ ፡ ወኢ ፡ በኢየሩሳሌም ፡ እስመ ፡ ይእቲ ፡ ሀገሩ ፡ ለንጉሥ ፡ ዐቢይ ። ወኢትምሐል ፡ በርእስከ ፡ እስመ ፡ ኢይትከሀለከ ፡ ትግበር ፡ አሐተ ፡ እምሥዕርተ ፡ ርእስከ ፡ ኢጸዓዳ ፡ ወኢጸሊመ ፡ አላ ፡ ይኩን ፡ ቃልክሙ ፡ እመኒ ፡ እወ ፡ እወ ፡ ወእመኒ ፡ አልቦ ፡ አልቦ ፡ ወዘፈድፈደ ፡ እምዝንቱ ፡ እምእኩይ ፡ ውእቱ ።

፩ሺ፮፻፰ ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ ዓይን ፡ ቤዛ ፡ ዓይን ፡ ወስን ፡ ቤዛ ፡ ስን ፡ ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ ኢትትቃወምዎ ፡ ለእኩይ ፡ በእኩይ ፡ ግሙራ ። ወለዘሂ ፡ ጸፍዐከ ፡ መልታሕቴከ ፡ ዘየማን ፡ ሚጥ ፡ ሎቱ ፡ ካልእታሂ ። ወለዘሂ ፡ ፈቀደ ፡ ይትዓገልከ ልብሰከ ፡ ኅድግ ፡ ሎቱ ፡ ክዳነከሂ ። ወለዘሂ ፡ ዐበጠከ ፡ ፩ደ ፡ ምዕራፈ ፡ ሑር ፡ ምስሌሁ ፡ ፪ተ ፡ ምዕራፈ ። ምዕራፍ ፡ ብሂል ፡ ብጽሐተ ፡ አንሥኦ ፡ ንጻሬ ፡ ወለዘሰአለከ ፡ ሀቦ ፡ ወለዘፈቀደ ፡ ይትለቃሕ ፡ እምኔከ ፡ ኢትክልኦ ። ሰማዕክሙ ፡ ዘተብህለ ፡ አፍቅር ፡ ቢጸከ ፡ ወጽላእ ፡ ጸላኢከ ። ወአንሰ ፡ እብለክሙ ፡ አፍቅሩ ፡ ጸላእተክሙ ፡

ስለ ፡ ብሉይና ፡ ሐዲስ ።

ላይ ፡ በከንቱ ፡ የሚቆጣ ፡ ሁሉ ፡ ቅጣት ፡ ይገባዋል ። ወንድሙንም ፡ ጨርቃም ፡ ወራዳ ፡ የሚለው ፡ የሸንጎ ፡ ቅጣት ፡ (ፍርድ) ፡ ይገባዋል ። ወንድሙንም ፡ ደንቆሮ ፡ የሚለው ፡ የገሃነም ፡ እሳት ፡ ተገባው ። መባዕህን ፡ ወደምሥዋዕ ፡ ብታመጣ ፡ ከዚያም ፡ የተጣላህ ፡ ወንድምህ ፡ እንዳለ ፡ ብታስብ ፡ መባዕህን ፡ ከዚያው ፡ ከምሥዋዑ ፡ ፊት ፡ ትተህ ፡ ሂድና ፡ አስቀድመህ ፡ ከወንድምህ ፡ ጋር ፡ ታረቅ ። ከዚህ ፡ በኋላም ፡ ተመልሰህ ፡ መባዕህን ፡ አግባ ።

፩ሺ፮፻፮ ለቀደሙት ፡ አትሰስኑ ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ሴትን ፡ አይቶ ፡ የወደዳት ፡ ሁሉ ፡ በልቡ ፡ አመነዘረባት ። ሚስቱን ፡ የሚፈታ ፡ ሰው ፡ የፍችዋን ፡ ደብዳቤ ፡ ይስጣት ፡ ተባለ ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ያለዝሙት ፡ ነገር ፡ ሚስቱን ፡ የሚፈታ ፡ ሰው ፡ ራሱ ፡ አመንዝራ ፡ አደረጋት ። የተፈታችዋንም ፡ ያገባ ፡ እነሆ ፡ አመነዘረ ።

፩ሺ፮፻፯ ዳግመኛም ፡ ለቀደሙት ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ። በሐሰት ፡ አትማል ። መሐላህንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መልስ ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ከቶ ፡ አትማሉ ። በሰማይም ፡ ቢሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ነውና ። በምድርም ፡ ቢሆን ፡ የእግሩ ፡ መረገጫ ፡ ናትና ። በኢየሩሳሌምም ፡ ቢሆን ፡ የታላቁ ፡ ንጉሥ ፡ አገር ፡ ናትና ። በራስህም ፡ አትማል ። ከራስህ ፡ ጠጉር ፡ አንዲቱን ፡ ነጭ ፡ ወይም ፡ ጥቁር ፡ ልታደርግ ፡ አትችልምና ። ነገራችሁ ፡ አዎን ፡ አዎን ፡ ወይም ፡ አይደለም ፡ አይደለም ፡ ይሁን ፡ እንጂ ። ከዚህም ፡ የበዛው ፡ (የወጣ) ፡ ከክፉ ፡ ወገን ፡ ነው ።

፩ሺ፮፻፰ ለቀደሙት ፡ የተባለውን ፡ ሰምታችኋል ። ዓይን ፡ የዓይን ፡ ቤዛ ፡ ነው ። ጥርስም ፡ የጥርስ ፡ ቤዛ ፡ ነው ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ክፉውን ፡ በክፉ ፡ ከቶ ፡ አትቃወሙት ። ቀኝ ፡ ፊትህን ፡ በጥፊ ፡ ለመታህ ፡ ሁለተኛዋንም ፡ መልስለት ። እጀጠባብህን ፡ ሊቀማህ ፡ ለወደደም ፡ መጐናጸፊያህን ፡ ተውለት ። አንድ ፡ ምዕራፍ ፡ ቢመልስልህ ፡ (ቢወስድህ) ፡ ሁለት ፡ ምዕራፍ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ሂድ ። ምዕራፍ ፡ ማለት ፡ ማየትን ፡ ማንሣት ፡ የሚደርስበት ፡ ነው ። (የዓይን ፡ አስተያየት ፡ የሚደርስበት ፡ ነው) ፡ ለለመነህም ፡ ስጠው ። ከአንተ ፡ ሊበደር ፡ የሚሻውን ፡ አት

### አንቀጽ ፡ ፵፮ ።

እዘ ፡ ወተወድሶ ፡ በከንቱ ፡ አላ ፡ በትሑት ፡ ልብ ፡ ወለይረሲ ፡ ለለ፩ዱ ፡ እምኔክሙ ፡ በጸ ፡ ዘእሁ ፡ ዘይኄይስ ፡ እምኔሁ ።

፩ሺ፯፻፹፰ መልእክተ ፡ ሐዋርያት ፡ ወዘሰ ፡ የአምር ፡ ገቢሮታ ፡ ለሠናይት ፡ ወኢይገብራ ፡ ኃጢአተ ፡ ትከውኖ ። ወአትሕቱ ፡ ርእሰክሙ ፡ ለኵሉ ፡ ፍጥረተ ፡ እንበለ ፡ እመሕያው ፡ በእንተ ፡ እግዚእን ።

### ስለ ፡ ከሐድያን ፡ ቅጣት ።

ክርክርንና ፡ በከንቱ ፡ መወደስን ፡ አታድርጉ ። በትሕት ፡ ልብ ፡ እንጂ ። ከእናንተ ፡ እያንዳንዱ ባልንጀራውን ፡ ከእርሱ ፡ የሚሻል ፡ ያድርግ ። (ፊል ፡ ፪ ፡ ፩ - ፫) ።

፩ሺ፯፻፹፰ የሐዋርያት ፡ መልእክት ። መልካም ፡ መሥራትን ፡ የሚያውቅ ፡ የማይሠራትም ፡ ኃጢአት፡ ትሆንበታለች ። (ያዕ ፡ ፬ ፡ ፲፯) ። ስለ ፡ ጌታችን ፡ ብላችሁ ፡ ለሰው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ራሳችሁን ፡ ዝቅ ፡ አድርጉ ፡ (፩ ፡ ጴጥ ፡ ፪ ፡ ፲፫) ።